# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፡ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 12 ነሐሴ 1 2000 ዓ.ም

## ጋዜጠኞች ስለ ግንቦት ሰባት እንዳይዘግቡ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው

## ሲ.ፒ.ጄ ድርጊቱን ተቃውሟል

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እየታተሙ ያሉ ጋዜጦች ስለ ግንቦት 7 ንቅናቄ የዜናም ሆነ የዘገባ ሽፋን እንዳይሰጡ በአገዛዙ ባለስልጣናትና ፖሊሶች ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው።የቁም ነገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ ታሰረ ዓለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ኮሚቴ {ሲ. ፒ. ጄ} ድርጊቱን ተቃውሟል።በተለየ መልኩ ስለንቅናቄው ሽፋን በመስጠት "ህዝብ ማወቅ አለበት"የሚለውን የጋዜጠኝነት ሙያዊ መርህ እየተወጣ ያለውና በአጭር ጊዜ ውስጥ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነው "አውራምባ ታይምስ" ሳምንታዊ ጋዜጣ ፤ዳግም ስለንቅናቄው አንዳችም ነገር እንዳይፅፍ በፖሊስ በባለስልጣናት ተከልክሏል፤እስከ ዛሬ ለሰጠውም ሽፋን ወደ ሰላሳ ገፅ የሚጠጋ የክስ ፅህፈት ተዘጋጅቶለታል።

ጋዜጣው፤ከትናንት በስቲያ ባወጣው ዕትሙ የዶክተር ብርሀኑ ነጋን ፎቶግራፍ በፊት ለፊት ገፁ የመጀመሪያ ስፍራ ትልቅ ቦታ ሰጥቶ በማተምና ከፎቶው ግርጌ "አውራምባ ታይምስ ስለንቅናቄው እንዳትዘግብ ተከለከለች" የሚል መግለጫ{ካፕሽን} በመፃፍ፤ በአጭሩ ዕውነታውን ለአንባቢዎቹ አሳውቋል።መቀመጫውን ኒው ዮርክ ያደረገው ዓለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት{ ሲ.ፒ.ጄ} ጉዳዩን አስመልክቶ ባውጣው መግለጫ የኢትዮጵያ ፖሊስ ባለስልጣናት እየፈፀሙት ያለውን ድርጊት ተቃውሟል።
የሲ.ፒ.ጄ የ አፍሪካ ፕሮግራም አስተባባሪ ቶም ሩድስ የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደንና ሌሎች አገር ቤት ያሉ ጋዜጠኞችን ዋቢ በመጥቀስ እየተፈፀመ ያለውን ድርጊት ከዘረዘሩ በሁዋላ፦"የተለያዩ ዲሞክራቲክ አስተሣሰቦችን ማንሸራሸር በሚያስፈልግበት አገር ውስጥ፤ፖሊስ ለጋዜጣ አዘጋጆች "ስለዚህኛው የፖለቲካ ጉዳይ ፃፉ፣ ስለዚህኛው ግን እንዳትፅፉ"እያለ መመሪያ የሚሰጥበት{የሚያስፈራራበት} ምንም መሰረት እንደሌለው ገልፀዋል።ቶም ሩድስ በማያያዝም ባለስልጣናት ከእንደዚህ ዓይነቱ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን ከሚፃረር ድርጊት እንዲቆጠቡና ጋዜጠኖች ስለሚፅፉት ነገር ምርጫውን ለራሳቸው ለጋዜጠኞቹ እንዲተውላቸው አሣስበዋል።

በሌላ በኩል የቁም ነገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ የቴዲ አፍሮ ጠበቃን የአቶ ሚሊዮንን ቃለ ምልልስ በማተሙ ከጠበቃው ጋር በእስር ላይ ይገኛል።ዋና መቀመጫውን ፓሪስ ያደረገው ድንበር የለሹ የጋዜጠኖች መብት ተሟጋች ድርጅት፣ ሲ.ፒ. ጄ እና ሌሎች ዓለማቀፍ ተቋማት በጋዜጠኛ መስፍን ዙሪያ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል።በቅርቡ የፀደቀውን የፕሬስ ህግ መቃወሙን በመግለጫው ያስታወሰው ሲ.ፒ.ጄ ፤ኢትዮጵያ በፕሬስ ነፃነት በኩል በጣም መጥፎ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር መሆኗን ጠቁሟል።
ከቅንጅት አመራሮች ጋር ታስረው በሚያዚያ 1999 ዓ.ም ከተፈቱት ስምንት ጋዜጠኞች መካከል፤የኢትኦጵና የዓባይ ጋዜጦች ባለቤት ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና እና የምኒልክ፣የአስኳልና የሣተናው ጋዜጦች ባለቤት እና በዓለማቀፍ ደረጃ ተሸላሚ የሆነችው ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል፤እንደሌሎቹ የሙያ ባልደረቦቻቸው በአዲስ መልክ በጋዜጣ ስራ ለመሰማራት ከበርካታ ወራት በፊት የፕሬስ ስራ ፈቃድ ቢጠይቁም እስካሁን ድረስ ሊሰጣቸው አልቻለም።የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ የቀድሞው ሀዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሲሆን ከቅንጅት አመራሮች ጋር ለ21 ወራት ታሰረው ከዋና አመራሮቹ ጋር በመጨረሻ ጊዜ ከተፈቱት ጋዜጠኞች አንዱ ነው።

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በስምንት ታላላቅ ከተሞች የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲቋረጥ ተደረገ

ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝብ በብዛት በሚኖርባቸው ስምንት ከተሞች ውስጥ የነበረው የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲቋረጥ ተደረገ።
"የኔት ወርክ አቅርቦቱ ውስን ስለሆነ የደረጃ ማሳደግ ስራ እስኪሰራ ድረስ" በሚል ምክንያት አገልግሎቱ የተቋረጠባቸውና በትንሹ ለቀጣዮቹ ሶስት ወራት የኢንተርኔት አገልግሎት እንዳያገኙ የተደረጉት ከተሞች ፦አዳማ፣ ነቀምት፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ሐረርና ድሬዳዋ ናቸው።
በመረጃና በግሎባላይዜሽን ዘመን "ኦቨር ሰብሰክሪብሽን" በሚል ምክንያት ጥንታዊና ታላላቅ ከተሞች ከአገልግሎቱ እንዲርቁ መደረጋቸው ያልተዋጠላቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ፣ ውስን ነው የተባለውን የኔት ወርክ አቅርቦት የማስፋቱና ደረጃ የማሳደጉ ስራ ከሶስት ወር ያላነሰ ጊዜ ይወስዳል መባሉ፤ እንዲሁም ለማስፋፋት ስራ ተብሎ በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ወቅት የስምንት ከተሞች አገልግሎት መቋረጡ የምክንያቱን ተዓማኒነት እንድንጠራጠር ያደርገናል ይላሉ።
ግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ በየሣምንቱ የሚያዘጋጀውን ድርጅታዊ ልሣን ኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኙት በብዙ ሽህ ወደሚቆጠሩት አባላቱና ደጋፊዎቹ ከሚያሰራጭባቸው የተለያዩ መንገዶች አንዱ ኢንተርኔት መሆኑ ይታወቃል።

## የግንቦት 7 የሬዲዮ ስርጭት በቅርቡ ይጀመራል

**ግንቦት 7 ንቅናቄ ወደ ኢትዮጵያ የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም በቅርቡ እንደሚጀምር የህዝብ ግንኙነት ክፍሉ አስታወቀ።**
**የፕሮግሙ ይዘት፤ሰአትና ፍሪኮንሲ በሚቀጥሉት የተወሰኑ ቀናት ውስጥ ለህዝብ ይፋ እንደሚሆን ንቅናቄው የገለጸ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ለአፈና የማይመች ጠንካራ ሬዲዮ ለመጀመር ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑ ታውቋል።**
**የሬዲዮኑን መጀመር በጉጉት የሚጠባበቁ ኢትዮጵያውያን በርካታ የደስታ መልእክቶችን ለንቅናቄው እየላኩ ሲሆን ዝግጅቱ ሲጀመር መልእክቶቻቸውን የምናቀርብ መሆኑን ከወዲሁ እንገልጻለን።**

# ርእሰ አንቀጽ

## በህግ አምላክ! ወድቃ በተነሳቸው ባንዲራ!

መብት እንዲከበር፣ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ህዝብ የሃገሩና የገዛ ህይወቱ ባለቤት እንዲሆን ለተደረገው ትግል፣ ወላጆች ውድ ልጆቻቸውን፣ ሚስቶች ባሎቻቸውን፣ ባሎች ሚስቶቻቸውን፣ እህቶች ወንድሞቻቸውን፣ ወንድሞች ደግሞ እህቶቻቸውን ገብረዋል፡፡ ትግሉ የመብት ብቻ ሳይሆን፣ ከድህነት፣ ከበሽታና ከመሃይምነትም ለመላቀቅ ነበር፡፡ ይሁንና ያ ሁሉ የእንባና የደም መባ ተከፍሎ የሃገራችን ህዝብ አልሞ ከተነሳውና በነጻነት ወዳድነቱ ለዘመናት ሲከፈለው ለኖረው መስዋእትነት የሚመጥን መንግስታዊ አስተዳደር መመስረት አልቻለም፡፡ ድህነትንና በሽታን የማጥፋት ህልሙ በኗል፡፡ ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የተከመረበትን የህይወት አሳርና መከራ ላጤነ፣ "እንዴት በአንድ ሃገር ህዝብ ላይ እንዲህ ማለቂያ የሌለው የመአት ዶፍ ይወርዳል?" የሚል የአግርሞትና የሃዘን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

ህዝብ ለህግ የነበረው ተስፋ ምን ያህል ስር የሰደደ እንደነበር በየአደባባዩ ወንጀልን፣ ጥቃትንና በደለን ለማስቆም፣ "በህግ አምላክ" የሚለውን የተደበዳይ ጩኸት እናስታውሰዋለን፡፡ ሌላው ተበዳይ ግለሰብ በአደባባይ ያሰማ የነበረው ጩኸት "ወድቃ በተነሳቸው ባንዲራ" የሚለው ነበር፡፡ ለአምስት የጣልያን ወረራ አመታት ነጻነቱን አጥቶ፣ በሃገሪቱ መናገሻ ከተማ የሃገሩን ባንዲራ ሳይሆን የፋሽት ጣልያን ባንዲራ ሲውለበለብ ያየ ህዝብ ለነጻነቱ መመለስ ከሰጠው ታላቅ ትርጉም ነበር ይህ አባባል የተወለደው፡፡ "ወድቃ በተነሳችው ባንዲራና በህግ አምላክ" ለኢትዮጵያ ህዝብ የነበራቸው ትርጉም አንድ ነበር፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደ ፍትህ ለነጻነቱ ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ በመሆኑ ተበዳይ፣ በዳይን በህግና በባንዲራ ስም መገዘት ይችላል የሚል ጠንካራ እምነት የነበረበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ "በህግ አምላክ! ወድቃ በተነሳቸው ባንዲራ አትንቀሳቀስ ብየለሁ" በሚል ትእዛዝ አንድ ግለሰብ ሌላውን ቀጥ አድርጎ ያስቆም እንደነበር የምናስታውስ ብዙዎች ነን፡፡ከሁሉ ባለይ ግን ሁላችንም የሃገሪቱን ተገዥዎች ለከፋ ሃዘንና ብስጭት የዳረገን፣ በህዝብ ቁስል ጭራሮ መስደድ የማያልቀበት የመለስ አገዛዝ ሰሞኑን በባንዲራ ስም የጀመረው ቧልት ነው፡፡ ትናንትና መለስ ዜናዊ የአምባገነናዊነትና የጸረ ኢትዮጵያ እምነቶቶቹ ውላጅ ከሆነው አመለካከቱ ተነስቶ ወድቃ የተነሳቸውን፣ የህዝብ የፍትህና የነጻነት ተምሳሌት የሆነቸውን ባንዲራ ‹ጨርቅ ናት› በማለት እንዳልተሳለቀብን ዛሬ፣ የባንዲራ ቀን የሚል በአል አዘጋጅቶ ያለ አንዳች ይሉኝታ ኑ አክብሩ ይለናል፡፡ ባንዲራ ለሀገር ዳር ድንበር የተከፈለ መስዋአትነት መገለጫ መሆኑ እየታወቀ፣ የሃገርን ድንበር በየአቅጣጫው እየቸበቸበ፣ መለስ ዜናዊ የባንዲራ ቀን ድግሴን አሙቁልኝ ይለናል፡፡

ይህ ትእይንት ግን ሶስት መቶ ሽህ ባንዲራዎች በመንግስት ኪሳራ እንዲያመርት ኮንትራት ከተሰጠው የመለስና የሸሪኮቹ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከሚያገኘው የትርፍ ጥቅም ሌላ የሚፈይደው አይኖረውም፡፡ ባንዲራን ማጣጣል በሰልጣን ላይ ለመቆየት ይጠቅመኛል ተብሎ በታሰበበት ወቅት ባንዲራን ማጣጣል፣ አሁን ደግሞ ያ የትም እንደማያደርስ በታየበትና ከስልጣን የመነቀል አደጋ ፊጦ በመጣበት ወቅት በስልጣን ከመሰንበት ስሌት ተነስቶ ባንዲራ ማውለብለብ ከተራ ብልጣብልጥነት ያለፈ ትርጉም እንደማይኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ይረዳዋል፡፡

እውነቱን ከሆነ፣ ወድቃ የተነሳቸው ባንዲራ ለህዘብ ትርጉም የምትሰጠው ህዝብ ላዳር ድንበሩ መከበር፣ ለነጻነትና ለፍትህ መስፈን ያለውን ቀናኢነትና ባለፈው የከፈለውንና ወደፊት ሊከፍለው የተዘጋጀውን መስዋእትነት የምትገልጽ ስለሆነች ነው፡፡ የሚወዳትም፣ የሚያፈቅራትም መለስ ጨርቅ ናት በሎ ሲጥላት እያነሳ ለእዚህ ያበቃትም ለእዚህ ነው፡፡ ይህንን ታሪካዊ፣ ሃገራዊና ህዝባዊ የባንዲራ ትርጎም ለአንድ አፍታ ሳይጋሩ፣ መለስና ጓደኞቹ የሚያውለበልቡት አረንጓዋዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለም ያለው ነገር በእነሱ እጅ ድሮም እነርሱው እንዳሉት ጨርቅ እንጂ ሌላ ትርጉም ከቶውኑ ሊኖረው አይችልም፡፡ የዛሬይቱ የሃገራችን ገዥዎች ህዝብ ለባንዲራ ያለውን ከበሬታ በእውን የሚጋሩ መሆናቸው የሚታወቀው፣ ባንዲራውን ስላውለበለቡ ሳይሆን፣ ከባንዲራው ጀርባ ለሚገኙት የህዝብ ፍላጎቶች ተገዢ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡ እነኚህ ፍላጎቶች የነጻናትና የፍትህ መስፈን ፣የብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም መጠበቅ ፍላጎቶች ናቸው፡፡ የመለስ አገዛዝ ደግሞ የማይታማበት ነገር ቢኖር እነዚህን የህዝብ ፍላጎቶች የማይጋራ መሆኑን ነው፡፡ በሀገራዊ ከህደት እየሰመጠ ነጻነትንና ፍትህን እየረገጠ የኢትዮጵያን ባንዲራ ለማውለብልብ የተነሱትን መለስንና ጓደኞችን ግንቦት7 "በህግ አምላክ፣ ወድቃ በተነሳቸው ባንዲራ" ባንዲራችንን ለቀቅ አድርጓት የሚላቸውም ለእዚህ ነው።

## "ለኢትዮጵያ መሪ ማን ይሁን የሚለውን እኛ አንወስንም፣ ያ የኢትዮጵያ ህዝብ ውሳኔ ነው"

አንድ የአሜሪካ ባከስልጣን

"እኛ ከማንም ጋር አንወግንም፣ለኢትዮጵያ መሪ ማን ይሁን የሚለውን እኛ አንወስንም፣ያ የኢትዮጵያ ህዝብ ውሳኔ ነው" ሲሉ አንድ ከፍተኛ የአሜሪካ ባለስልጣን ትኛንት ገለፁ።የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ረዳት-ሚኒስትር ዴቪድ ክሬመር በኢትዮጵያ የግንቦት 97ቱን ምርጫ ተከትሎ የታየው ሁኔታና በቅርቡ በፕሬሱና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ዙሪያ እየወጡ ያሉት ህጎች አገራቸውን እያሣሰባት እንደሚገኝ ገልፀዋል።

"በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያን በጎበኙ ወቅት ስጋቶቻቸውን በሙሉ ለአቶ መለስ መግለፃቸውን ያስታወሱት ዴቪድ ክሬመር፣" ነገሮችን በጥንቃቄ መመልከታችንን እንቀጥላለን" ብለዋል።"የኛ ፍላጎት የኛን ወይም የሌላን መንገድ በግድ በኢትዮጵያ መንግስት ወይም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለመጫን አይደለም።ውሳኔው የነሱ ነው።አንዳንድ ያሣሰቡን ነገሮች ግን አሉ።ሰብዓዊ መብትንና ዲሞክራሲን በተመለከተ በአገሪቱ ጠንካራ መሰረት እንዲኖር እንፈልጋለን።ወደ ኢትዮጵያ የተጓዝኩትም በዚህ ዘሪያ ዋሽንግተን ያላትን ስጋት ለመግለፅ ነው" ሲሉ ተናግረዋል ረዳት-የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ።

ባለፈው ሚያዚያ በኢትዮጵያ በተደረገው የማሟያ ምርጫ ከ3 ነጥብ 6ሚሊዮን መቀመጫዎች፣ተቃዋሚዎች ሶስት ወንበር ብቻ ማግኘታቸውን እንደተመለከቱ የጠቆሙት ክሬመር፣" ለዚህ ምክንያቱ ንም ሰምቻለሁ፣ውጤቱ የሚያስደምም ስሌት ወይም አህዝ ነው" በማለት እጅግ መገረማቸውን ገልፀዋል።ረዳት-የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በማጠቃለያቸውም፦" ለኢትዮጵያ መሪ ማን መሆን እንዳለበት መወሰን የኛ ጉዳይ አይደለም።ያ የኢትዮጵያ ህዝብ ውሳኔ ነው።እኛ ከማንም ጋር አንወግንም" በማለት የአገራቸውን አቋም ይፋ አድርገዋል።

**ኩሩ ህዝብ ነን!**
**አገራችንን እናድን !**
**መብታችንን እናስከብር!**
**እንተባበር! እንነሳ! እንታገል!**
**እንደ ቀደምቶቻችን ታሪክ እንስራ**

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## “የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ”

ጋቹዬ

ዓለማቀፉ ዓቃቤ ህግ የሱዳኑን ፕሬዚዳንት ኦማር ሐሰን አልበሽርን ለመክሰስ ዘ-ሔግ ለሚገኘው ፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረቡን ተከትሎ ፤የተወሰኑ የአፍሪካ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፤ ሰሞኑን አዲስ አበባ ላይ ባደረጉት ስብስባ፤-ከየጌቶቻቸው የተላለፈላቸውን የተቃውሞ አቋም አሳልፈዋል።በተለይ አቶ ስዩም መስፍን በዚህ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር፦”አፍሪካ በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ትቃወማለች…ዓለማቀፉ ዓቃቤ ህግ በሱዳኑ ፕሬዚዳንት ላይ ያሳለፈው አቋም-የአንዲትን አገር ሉዓላዊነት የሚጋፋ ሰለሆነ እንቃወመዋለን” ብለዋል። አቶ ስዩም የተናገሯቸውን ሁለት ታላላቅ ነጥቦች ልብ በሉ-1-ሰብዓዊ መብት 2-ሉዓላዊነት።

አፍሪካ፤በዓለማችን የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች በአስከፊ ደረጃ የሚገሰስባት አህጉር ናት።ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በየጊዜው ወደ ስልጣን የሚወጡ ቡድኖች፤ አንዴ ከያዙት ወንበር የመልቀቅ ፍላጎቱም ሀሳቡም ስለሌላቸውና እንደ ርስት የሚቆጥሩትን ስልጣናቸውን ለማቆየት ይረዱናል ብለው የሚያምኑባቸውን ማናቸውንም እርምጃዎች በአገርና በዜጎች ላይ ስለሚፈፅሙ ነው።

…ስለዚህም የዜጎች የመብትና የነፃነት ጥያቄዎች እስኪረጋገጡ ድረስ፤ህዝባዊ አመፅ ሊቀጥልና ሊቀጣጠል ግድ ይሆናል።’ነፃነት በነፃ አይገኝም” ያለው ማን ነበር?አዎ! የአቶ ስዩምን የእብደት አባባል ካጤናችሁት፤በማያሻማ ቋንቋ እነዚህ አምባገነኖች መወገድና መወገድ ብቻ እንዳለባቸው እንስማማለን። እነዚህን፤እያሉት ካለው ነገር በመነሳት ስንለካቸው፤በዳርፉሩ ግጭት ፤እንኳን 200 ሺህ ሰው፤200 ሺህ ብርም የጠፋ አልመሰላቸውም።ግን “የፖለቲካው መዝገበ-ቃላት አንድ ሆነና” ስለተከበረው የሰው ልጅ መብት ለመናገር ደፈሩ። “ሰብዓዊ መብት”አሉ። እንዴ?! የት የምታውቁትን ሰብዓዊነት አቶ ስዩም? ነፍሰ- ገዳይ-ስለ ሰብዓዊ መብት እንዲያወራ ሊቸንሳ የሰጠው ማን ነው? “የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ”የሚለውን የመፅሐፍ ቃል አላነበቡትም እንዴ? እባክዎ ያንብቡት አለያም ዶክተር ጳውሎስን ያስነብቡ።በዚህ ከተስማማን እቀጥላለሁ፦

አቶ ስዩም! ልቀጥል እየሰሙኝ ነው? በየጊዜው በድብቅ እየታፈኑ የሚሰወሩትና በፍትህ ስም የሚወገዱት ይቆይልንና በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በጋምቤላ፣በሲዳማ፣ በቦረና፣ በደሴ፣ በባህርዳር፣ በአምቦ … ፣ ስንት ሺህ ሰው በላችሁ?ስንት ሺህ ሰውስ አሰበላችሁ? ስለ ሰብዓዊ መብት የማታወሩት የምትገሏቸው ብቻ ሳይሆን የምትበሏቸው ሰዎች ቁጥር ስንት ሲደርስ ነው- እናንት በላዔ ሰቦ’ች?!

ዲሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶችን ከስማቸው ባሻገር የማታውቁ እናንት ደረቅ ምንቹች! እየሰማችሁኝ ነው? በስልጣናችሁ ማግስት በየከተማው በስንት ወጣት ላይ ኢላማ ተለማመዳችሁ?በ1984 እና በ1993 ስንት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን መታችሁ?ሰኔ1-1997 እና ጥቅምት 22-1998 ዓ.ም የስንት ህፃናትና ወጣቶችን ደም ጠጣችሁ?ስንቱን ቤት በሀዘን አጨለማችሁ? አቶ ስዩም ተናግረው አያናግሩኝ?

የእርስዎ ስለሰብዓዊ መብት ማውራት-እሪያ -መቅደስ ለመግባት የደፈረች ያህል ስለተሰማኝ ነው የሞገትኩዎ።ምክንያት?**መፅሐፉ ስላዘዘኝ** ምን ብሎ? **“የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ!”ብሎ**።ሌላው አቶ ስዩም በድፍረት የተናገሩት ሳይሆን ያረከሱት ነገር ቢኖር-“ሉዓላዊነት”የሚለውን ቅዱስ ቃል ነው።ኢትዮጵያውያን በዴሞክራሲ ስም በጠመንጃ መረገጥ ከጀመሩ፣በህግ የበላይነት ስም ፍትህን ካጡ፣በነፃ ገበያ ስም

ከተዘረፉ፣በልማት ስም ለረሀብ ከተዳረጉ፣በመድብለ ፓርቲ ስም ፍላጎታቸውንና ምርጫቸውን ከተነፈጉ፣በአጠቃላይ የዜግነት ሉዓላዊ መብታቸውን ከተገፈፉ ጥቂት የማይባሉ ዓመታት አለፉ።ጎደሎውህገ-መንግስት ሳይቀር፦”የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች የህገ-መንግስቱ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤቶች ናቸው”ቢልም፤በተግባር ደረጃ ህግም ዳኝነትም አንድ ሰው ሆኖ የዜጎች ሉዓላዊነት በከፋ ደረጃ እየተረገጠ ይገኛል።

አቶ ስዩም !እየሰሙኝ ከሆነ ተፈትናችሁ የወደቃችሁት የዜጎችን ሉዓላዊ መብት በመጨፍለቃችሁ ብቻ አይደለም።እንደ አገርም ታፍሮና ተከብሮ የቆየውን የአገሪቱን ሉዓላዊ ግዛት እንደ ጋለሞታ የደፈራችሁና ያስደፈራችሁ የፖለቲካ ሴሰኞች ናችሁ።

ለጊዜው ሌሎቹ ይቆዩልንና በባድመ ዙሪያ ከኤርትራ መንግስት ጋር በገባችሁት ጦርነት በ10 ሺህዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በማታውቁት “ሉዓላዊነት ስም” ማገዳችሁ።ከጦርነቱ በሁዋላ ነገሩን ይግባኝ በማይጠየቅበት ፍርድ ለመጨረስ ተስማማችሁ።ፍርድ ቤቱ፤ ባድመንና ሌሎች ቦታዎች ጭምር ለኤርትራ እንዲሰጡ ወሰነ።እርስዎም ተንደረደሩና፦”ባድመ ለኛ ተወሰናለችና እልል በሉ” በማለት የዋሁን ወገኔን መስቀል አደባባይ የድጋፍ ሰልፍ አሰወጡት። (አሁን አሁን ያ ጉድዎ ትዝ ሲልዎት ምን ይሰማዎት ይሆን?) ምርጫ 97ን አስመልክቶ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በሸራተን ሆቴል”በውጭ ግንኙነት ፖሊሲ”ዙሪያ ለፓርቲዎች ባዘጋጀው መድረክ ኢህአዴግን ወክለው ቀረቡ።ቅንጅትን በመወከል የቀረቡት ዶክተር ያዕቆብ ሀይለማርያምም፦”… ባድመ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ለኤርትራ ተሰጥታ ሳለ፤እርስዎ ባድመ ለኛ ተወሰነች ብለው መግለጫ መስጠትዎ፤አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፍርድ ቤት ውሳኔን አንብቦ ለመረዳት ያለበትን ችግር የሚያሳይ ነው”ሲሉዎት፤አጋጣሚውን ተጠቅሞ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ ምን ችግር ነበረበት?ሌላው ቢቀር አለቃዎ”የአክሱም ሐውልት ለደቡቡ ምኑ ነው ብለዋል ወይ?”ተበለው ሲጠየቁ {ምንም ባይሳካላቸው} ለመተጣጠፍ ያደረጉትን ሙከራ መኮረጁ ማንን ገደለ? እርስዎ ግን ያስወሰዱት’ ትርፍ ስጋ ‘ይመስል፤ዘለው “ዘራፍ!”አሉ።የሉዓላዊነቱ ጥያቄ ተራ ጉዳይ ይመስል ፤ሃሳብ ሲያጥርዎ እንደልማድዎ ከንፈርዎን እየበሉ በንዴት፦”እንኳን!እንኳን! ደግ አረኩ!” ብለውን አረፉ። ታዲያ ዛሬ ስለ ሉዓላዊነት ሊነግሩን እንዴት ደፈሩ?የት የሚያውቁትን ሉዓላዊነት አቶ ስዩም?ሌላው ቢቀር በድብቅ ለሱዳን ቆርጣችሁ በሰጣችሁት አንድ አገር የሚያህል መሬት ዙሪያ፤ ከጫፍ እስከ ጫፍ ህዝብ እየጮኸ ባለበት በአሁኑ ወቅት ስለ ሉዓላዊነት ሲናገሩ፤ ሳግ አልተናነቀዎትም? ስቅታ አልረበሸዎትም? ተፈትቶ የማያውቀው ምላስዎ ይበልጥ አልተያያዘብዎትም? አልዋሸዎትም፣ እርስዎ ሉዓላዊነት ስላሉ፤ የእኔን አፍ ደም ደም ብሎታል። ባሪያሻጮች ስለ ነፃነት፣ ከሀዲዎች ስለ እምነት፣ አመንዝሮች ስለ ቅድስና፣ ገዳዮች ስለ ርህራሔ እንዲነግሩኝ አልፈቅድማ።

አዎ!እናንተ ስለሰብዓዊ መብትም ሆነ ስለ ሉዓላዊነት የምታወሩበት አንዳችም የሞራልም ሆነ የህግ መሰረት የላችሁም። እስከዛሬ ያለ አግባብ ብዙ ነገሮቻችንን ወስዳችሁብናል። እኛም በዝምታ ቆይተናል።ወደፊትም፤ ታሪክና አጋጣሚ የሰጣችሁን ዕድል ልትጠቀሙበት፣ቦታውን ልታውቁበት እንደማትችሉ አረጋግጠናል።ስለዚህም የነጠቃችሁንን ለማስመለስ ተነስተናል።ዜግነታዊ መብትንና ኢትዮጵያን ታህል አገር ለእናንተ ብቻ ሰጥቶ ዝም ማለት ወንጀል ነውና።ምክንያት?**መፅሐፉ ስላዘዘን** ምን ብሎ?**“የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ”** ብሎ።

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## የዘንድሮውስ ልዩ ነው፣ለደብተራ መላእከሰላምና ለግንቦት 7፣

የኢህአዴግ ጋዜጠኞች በዜናዎቻቸው ላይ "የዘንድሮውን እንትን ልዩ የሚያደርገው" ብለው ካልዘገቡ ጌቶቻቸውን ያስደሰቱ አይመስላቸውም፤ "የዘንድሮውን ሚሊኒየም ከቀድሞዎቹ ሚሊኒየሞች ልዩ የሚያደርገው... "ወይም የዚህ አመት የጤፍ ምርት ከቀድሞዎቹ የሚለየው..." የሚሉትን ዜናዎች በተደጋጋሚ በእየምሽቱ ያሰሙናል።ይህ "የልዩ ነው" ዜና ምን ያክል እንዳስመረረን ምናልባት ውጭ አገር የምትኖሩት አታውቁት ይሆናል እንጅ እኛ በአገር ቤት እየኖርን አማራጭ ያጣነዎቹ አውርተን የጨረስነው ነው ። በህወሀት ዘመን ሁሉም ነገር ልዩ ነው።በቆሎው ልዩ ነው፣ጤፉ ልዩ ነው፣ፋሲካው ልዩ ነው፣ጠላው፣አረቂው፣ ዲሞክራሲው ምናለፋችሁ ሁሉም ነገር ልዩ ነው።

አንድ ጊዜ፣ በየወሩ እየመጣ የሚጎበኘኝ ደብተራ፣ የመንግስቱ ጋዜጠኞች የሚያነቡትን ዜና ሰማና "የዘንድሮውን ረሀብ ከቀድሞዎቹ ረሃቦች ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው ብሎ ጠየቀኝ"። መልሱ ግራ ሲገባኝ ምን ለማለት ፈልገህ ነው አንተ አልኩት። "እነዚህ ሰዎች ለሁሉም ነገሮች ልዩነትን እየፈለጉ ሲናገሩ ለረሀቡና ለኑሮ ውድነቱ ግን ልዩነትን መፍጠር የቻሉ አልመሰለኝም" አለኝ። በል እነሱኑ በድብዳቤ ጠይቃቸው ብየው የጨዋታውን ርእስ ቀየርኩበት። ከሶስት ወራት በሁዋላ ከህወሀት መንደር ያገኘሁት መልስ ነው ብሎ የሚከተለውን ጽፎ ላከልኝ።"የተከበርከው ወዳጄ" ይላል መግቢያው ፣"ጥያቄየን ለህወሀት የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ክፍል በላክሁት መሰረት የሚከተለውን መልስ አግኝቻለሁና በጽሞና አንብበው" ።

"የዘንድሮውን ረሀብ ከወትሮዎቹ ረሀቦች ልዩ የሚያደርገው፡

*1ኛ፣ ለአራት ተከታታይ አመታት 10 በመቶ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በታየበትና ህዝባችንን ለልማት ባሰለፍንበት ወቅት መምጣቱ*

*2ኛ፣ ኤክስፖርት መር የልማት ስትራቴጂያችን የፈረንጅ ገበያዎችን ባጥለቀለቀበት ሰአት መገኘቱ*

*3ኛ ከህወሀት የ17 አመታት አገዛዝ በሁዋላ የተገኘ ድል መሆኑ*

*4ኛ ረሀቡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን መጎብኘቱን ትቶ መላውን የአገሪቱ ክፍሎች ለማካለል መቻሉ*

*5ኛ፣ የሚሊኒየሙን በእል በከፍተኛ ወጪ እና ድምቀት እያከበርንበት ባለንበት ሰአት መምጣቱ*

*6ኛ፣ በሶማሊያ ወረራ ሰራዊቱና የአገሪቱ መሪዎች ተወጥረው በሚገኙበት ሰአት የተገኘ አኩሪ ታሪካዊ ድል መሁኑ*

*7ኛ፣ የአገሪቱ የመከላከያ በጀት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር በተደረገበት ማግስት መምጣቱ*

*8ኛ፣ ከኤርትራ ጋር ለማይቀረው ጦርነት በምንዘጋጅበት ማግስት የተገኘ መሆኑ*

*9ኛ፣ በርካታ አርሶአደሮች፣ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የምርት ዘመቻን ትምህርት በመቅሰም ሚሊየነሮች በሆኑበት ሰአት መገኘቱና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጧቸውን ሽልማት አይተው ሳይጠግቡ የመጣ መሆኑ*

*10ኛ፣በኦጋዴን፣በኦሮሚያና በሌሎች ቦታዎች በሚደረጉ ጦርነቶች፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ተቃዋሚዎችን እንደሚረዱ አስተማማኝ መረጃ ባገኘንበትና መረጃውን መሰረት አድርገን ህዝቡ ፊቱን ወደ ምርት እንዳያዞር አፍነን በያዝንበት ወቅት የመጣ በመሆኑ የዘንድሮውን ረሀብ ከዎትሮዎቹ ረሀቦች ሁሉ ለየት እንደሚያደርገው እንገልጻለን።የኢህአዴግ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ክፍል፣የማይነበብ ፊርማ አለው።"*

የጻፈው ምን አስቦነው አልኩና ቶሎ ብየ ወረቀቱን ቀዳድጄ አቃጠልኩት።ማን ይታመናል ዘንድሮ? ለነገሩ ደብተራ መላከን "የጌታ ሎሌ፣ለሰማዩ እንጅ ለምድር ጌታ የማይገዛ" እያለ ዘወትር ሲፎክር ስለምሰማው በቀላሉ እጅ እንደማይሰጥ አምነዋለሁ። ያን ጊዜ፣በግንቦቱ ምርጫ ወቅት ማለቴ ነው፣ደብተራ መላከ በቀሳውስቱ ውስጥ ያለውን የቅንጅት ደጋፊ እንዲጠቁምና ገንዘብ እንዲሰጠው ቢለመን የሰማዩ ቤቴ ይበልጥብኛል ብሎ እምቢ ማለቱን አገር ሁሉ ያውቅለታል። የደብተራ መላእከ ሰላም ጭንቀት እረፍት እየነሳ ሲያስቸግረኝ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፌ አንዱን ለእርሱ ግልባጩን ለግንቦት 7 ላክሁት። በነገሬ ላይ፣ የግንቦት 7 ትን የስላሴ ጸበል ቅመሱ እየተባለ መጠራራት መጀመሩን ሰምታችሁልኛል? የመርካቶዋን አሮጊት ታሪክስ? አሮጊቷ ሲምሉ "የግንቦቱ ስላሴ" ሲመርቁ ደግሞ ፣የግንቦቱ ስላሴ ይገላግልህ" ይላሉ እየተባለ ይወራል። ይቅርታ የተላከውን ደብዳቤው እረሳሁት። እንዲህ ይላል፣" ይድረስ ለደብተራ መላእከ ሰላም ወልደ ዘ አማኑኤል ። ዘንድሮ ረሀብና የኑሮ ውድነቱ መክፋቱን ከደንበኞችህ ሳትሰማ አትቀርም።ጤፍ እንጀራ ከበላን ከርመናል።በቆሎን እንጀራ ሁን ብንለው፣ጤፍ ያዝንብኛል ብሎ ከምጣዱ አልወጣም አለን። አሁን ከእኛ የባሰው ደሀ አስር ኪሎ በቆሎ በየወሩ በ600 መቶ ብር ሂሳብ እንዲሰጠው መመሪያ ወጥቷል። ጋዜጠኞችም፣'የዘንድሮውን አመት ልዩ የሚያደርገው መንግስት እህል በገፍ እና በርካሽ ዋጋ ለህዝቡ ማከፋፈል መጀመሩ ነው' ብለው አውርተዋል።ይህን ቴሌቪዥን ልሸጠው አስብና አንዳንዴ የደጀሰላሙ ወሬ ሲሰለችህ ዘመንኛ ወሬ መስሚያ እንዳታጣ ብየ መልሸ እተወዋለሁ።

እኔን የሚገርመኝ እርሀብ በቁመናችን ሲበላን እያየን በሚያስርቡን ገዚዎች ላይ ለማመጽ እስካሁን አለመቻላችን ነው።ድሮ ከረሀብ ጥይት ይሻላል ይባል ነበር።አሁንስ ጥይቱን እየፈራነው ነው መሰለኝ ሲርበን አንጮህም። ደግሞስ ስንቱን ገድለው ሊጨርሱት ነው? እኛ ከተደራጀንባቸው እነሱ ምን ሀቅም አላቸው፣አገር እንደሆን ጠልቷቸዋል። እንደኛ ኑሮ የተወደደባቸው የሌሎች አገሮች ህዝቦች በመንግስታቸው ላይ ማመጻቸውን በቅርቡ ሰምተናል።ሀይቲ በምትባል አገር ህዝቡ በአመጽ ጠቅላይ ሚኒስትሩን አባሯል፤በባንግሊያዲሽ፣በትሪኒዳድና ቶቤጎ፣በኮትዲቯአር፣በሴኔጋል፣በፊሊፒንስ፣በቡርኪና ፋሶ፣በሞሮኮ፣በካሜሩን፣በየመን፣በፓኪስታን፣በኢንዶኔዢያ፣በሞሪ ታኒያ፣በኡዝቤኪስታን እና በጎረቤታችን ኬንያ ህዝቡ በመንግስቱ ላይ ያለውን ተቃውሞው አሰምቷል። የእኛ ሰው ግን ነገሩን በሆዱ እየያዘ ዝምታን መርጧል።

ሰሞኑን የታንኩን መርመስመስ በቴሌቪዥን እያየ ሰው ማጉረምረም ጀምሮዋል አሉ። በርሀብ ላይ ጦርነት? ምነው ህዝብ በዝቶ አላልቅላቸው አለ? እየተባለ ነው ። እንዲያውም አንድ ጠንካራ መሪ ተነስ እስከሚለው እየጠበቀ ነው እንጂ ህዝቡ ለመነሳት በቋፍ ላይ ነው።አንተም በእየደጀሰላሙ ቀስቅስ።17 አመት ሙሉ ለውጥ ይመጣል ብለን ብንጠብቅ ጠብ የሚል ለውጥ የለም።በግንቦቱ ምርጫ የለውጥ ተስፋ ብናይም፣ሳይፈጸም ቀረ።አሁን ክንዳችንን ማስተባበር ይኖርብናል።መሪ እንኳን ብናጣ አንተ መሪ እኔ ተመሪ እየሆንን፣ወይም ሁለታችንም እየመራን እና እየተመራራን ትግላችን መቀጠል አለብን።እኔ ለራሴ በቃኝ ካልኩ ቆይቻለሁ። ልብ ብለህ ስማኝ ደብተራ መላከ፣እኔን በእየምሽቱ ብቅ እያልክ 'ምን ተባለ ዛሬ?' እያልክ ወሬ ከምትጠይቀኝ፣ዛሬ ምን ሰራሁ ብለህ እራስክን ጠይቅ።ሌሎች ታሪክ እስኪሰሩልህ አትጠብቅ፣አንተው ላንተው ሁን፣ሌሎችም ለራሳቸው ይሁኑ።ለሚጠይቁህ ደንበኞችህ እራሳችሁን ሁኑ ብለህ አስተምር። እንዲያ ከሆነ በአጭር ጊዜ ለለውጥ እንነሳለን።የለውጥ ሰአቱ ደርሷል።አደራህን ተኝተን እንዳንገኝ።"

አክባሪህ እርሱ ታለ ማንተጋፍቶት፣ከቄራ ሰፈር፣አዲስ አበባ።